ከPO2 ፍሬሰናይ ከበደ ገብረየስ (የቀድሞ የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል አባል)

በትዝታ ዓለም ወደኋላ ተመልሶ ክፉም ይሁን ደግ ነገር ሲታወስ ሃዘንም ይሁን ደስታ የሕይወታችን ነጸብራቅና በሃገራችን ሕብረተሰብ ታሪክ ውስጥ አንዱ የማንነታችን ገጽታችን ነው።

ይህን ሊያሳስበኝና ሊያነሣሳኝ የቻለው ጉዳይ ከታዳጊነት እስከእውቀት አብረን በኢትዮጵያ የባሕር ኃይል አባልነት በጽናት ያገለገልን ጓደኛሞች ስለሃገራችንም ሆነ ስለራሳችን የለፋንበትን የደከምንበትን ውጣ ውረድ በተገናኘን በተወያየን ቁጥር ዋናው ርእሰ ጉዳያችን የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል ትዝታዎች ናቸው። በተለይም ብዙ ውድ ወንድሞቻችን የወደቁበት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1982 ዓም በምጽዋ የተደረገው ከባድ የጦርነት ውሎና
አንድም ጊዜ በውጭ ወራሪ ኃይል የባሕር ክልላችን ሳይደፈር ያገለገልንበት የባሕር ላይ ወታደራዊ ግዳጅ ውሎዋችን ነው።

ኢትዮጵያ ሃገራችን ወደብ አልባ ከሆነችበት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር እስከ1991 ድረስ፡ የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል ከተቋቋመበት ከ1948 ዓም ጀምሮ ከሌሎቹ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ምድር ጦርና አየርኃይል ጋር የባሕር ኃይላችን ኢትዮጵያ ሃገራችንን ድንበሯን ቀይ ባህሯን በውጭ ወራሪ ሳያስነካና ሳያስደፍር የነበረ አንዱ ክፍል ነበር። ይህንን በተመለከተ ከሁለት ዓመት በፊት በ762 በያዘ ገጽ * ኢትዮጵያ የባሕር ጠረፏና ባሕር ኃይሏ* በሚል አርእስት ኢትዮጵያ ጥንታዊው የባሕር ንብረቷ እስከቅርብ ጊዘ ድረስ ባለባሕር ሃገር መሆኗን ታሪኳን ግልጽ ባለ መልኩ የቀረበና ለአዲሱ ትውልድና ቀደም ብሎም ኢትዮጵያ በጥንት ታሪኳና የባሕር ሰፊ ክልል እንዳላት ለተምታታበት ኢትዮጵያዊ ግልጽ ባለ ሁኔታ የሚያስተምር ግንዛቤን የሚያስጨብጥ መጽሃፍ ሲሆን፡ በባሕር ኃይል አባልነት በአገልግሎት ዘመናችን ስለነበረው አንዳንድ ሁኔታዎች ከቅርብ የባህር ኃይል አባላት ከነበሩ ጓደኞች ጋር ስንወያይ፡ በዚህ መጽሃፍ ውስጥ ከቀረቡት የቅርብ ጊዜ  በተለይም በ1982 በምጽዋ የነበረውን ከባድ የጦርነት ዘገባና፡ሌሎችም ቅር የሚያሰኙና ስህተት የሆኑ ሁኔታዎችን ሳናነብና ስንወያይ ግር የሚሉ ከእውነታ ውጭ የሆኑትን እንዴ ይኼማ ልክ አይደለም እንዲህ ነበር በማለት በአይኔ ካየኋችሁና በመጽሃፉ መቅረብ ያለበትን አዘጋጆቹ በሕይወት ያሉትን የምድር ጦርም ይሁን የባሕር ኃይል አባላት አፈላልገውና አወያይተው ለምን በጥንቃቄ እንዲጻፍ አላደረጉም የሚል ቀጥተኛ ውይይት እያደረግንና እየተቸንም ይሁን እያዘንን እንገረም ነበር። በየአመቱ የባሕር ኃይል ቀን ሲከበር፡ ቀደም ብሎ ፖለቲካ መምሪያ የሚባለው ክፍል ከሚያሳትመው መልህቅ መጽሔት ጋር የሚመሳሰሉ ሁኔታዎችን አስተውዬበታለሁ። በባሕር ኃይል ቀን መጽሔቱ ሲታደል፡ አብዛኛውን የሚዘግበው በማንኛውም የጦር ክፍል አሰልቺ የሆነውን ወይም የነበረውን የቀድሞውን የማርክሲስት ርእዮትና ተደጋጋሚ የቀደምት የባሕር ኃይልን ምስረታ ነበር። ከአለም የሳይንቲስቶች አንድነት ይካተታሉ የሚባሉት የባሕር ኃይል ኮሌጅ ሕንዳዊው አስተማሪ ፕሮፌሰር ማቲው የሚባሉ ይመስለኛል ስማቸው ባልሳሳት፡ የሚዘግቡት ጥናታዊ ጽሁፍን ማንበብ አስተማሪና የሚስብ ቁም ነገሮች ነበሩበት።  የቀደምት የባሕር ኃይል አለቆቻችንና ጓደኞቻችን የምጽዋውን ከባድ የምድር ውጊያ በግዳጅህ ወቅት ያየኸውንና በራስህ በኩል ስለነበረው ከምታስታውሳቸው የሚሰማህን ለምን አትጽፈውም የሚል ከአብዛኛዎች የባህር ኃይል ባልደረባዎች ሃሳብ ይነገረኝ ነበር። ከማስታውሳቸው ሁኔታዎች ትዝ የሚሉኝን ሁሉ እናወጋ ነበር። እየቆየ ሲሄድ ይረሳልና ጻፈው የሚል ሃሳብ ይቀርብ ስለነበርና፡ በተለይም የአመራር ጉድለት ሰራዊቱን ለሽንፈት የዳረገው ግልጽ ነገሮችን በአይናችን ያየነውንና ይሄ ነገር እንዲህ ቢሆንስ ተብሎ ለዋናዎቹ የጦር መሪዎች ከበታች ሃሳብ ቀርቦ ተቀባይነትን አጥቶ የነበሩትን ሁኔታዎች ስናስታውስ የቁጭትና መሆን ነበረበት የሚለውን ውይይት ማድረግ ታላቅ የራስ ምታትንና ሃዘኔታን ያስታውሰናል።
ጦርነቱን በተመለከተ በውጊያው ላይ የነበረው የ50 አለቃ ታደሰ ሳልቫኖ * አይ ምጽዋ * በሚል ስያሜ ያቀረበውን መጽሃፍ ሳነበው፡ ከጅማሬው እስከፍጻሜው እያዘንኩና የወደቁትን የቆሰሉትን በሕይወት ያሉትን ሁሉ በማስታወስ የማይጠፋውን ትዝታ ሁሉ ስቃኝ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የባሕር ኃይላችንን የውጊያ ውሎ በአንድ የምድርጦር አባል እውነታው ሲቀርብ በማንበቤ ከልብ አመሰግነዋለሁ። በባሕር ክልላችን ስናደርግ የነበረውን ግዳጅ በጥቂቱም ቢሆን በጉዞ መልክ ያዩ የምድር ጦርና አየር ኃይል ባልደረቦች ሊናገሩ ሲችሉ፡ ከላይ ከጄነራል ማእርግ አንስቶ እስከታች ድረስ ያሉ አባላት፡ ባሕር ኃይልማ ተቀምጦ የሚኖር የጦር ክፍል እንጂ፡ ምን ሰራ እያሉ በድፍረት ሲናገሩ መስማት፡ እንገረምም ነበር ባለማወቅ ብዙ ሊባል ይቻላል። በመሃል ሃገር የሚኖረውም ሕብረተሰባችን ባሕር ኃይልን የሲቭል መስሪያ ቤት እየመሰለው፡ ከመብራት ኃይል መስሪያ ቤትና ከንግድ መርከብ ኩባንያ ጋር እያመሳሰሉ ሲጠይቁን አብራርተን ለማስረዳት እንጥር ነበር።  የምድር ውጊያ በባሕር ኃይል የማሪን ኮማንዶ አባላት በዋናነት ሙያ የተማሩት ቢሆንም መርከበኛው ክፍል በመሰረታዊ የምድር የአንድ የመቶ አሰላለፍ(ASULT) ታክቲክ በባሕር ማሰልጠኛ ቀደም ብሎ ይሰጥ ነበር። ወደመጨረሻው አካባቢ የነበሩት የባሕር ኃይል አባላት ግን ይህን ትምህርት ባይሰጣቸውም የነፍስ ወከፍ መሳሪያዎችን የምእራብ ሃገሮችንንና የምስራቅ እንዲማሩ የባሕር ኃይላችን በሚገባ ሲያስተምረን ቆይቷል። በባሕር ኃይል አባልነታችን ዋናው

ግዳጃችን ቀይ ባሕርን ከውጭ ወራሪ ኃይል መከላከልና ማስከበርና በባሕር ጠረፍም ለምድር ጦሩ የመድፍ ድጋፍ መስጠትና በምድረነክ የጦር መርከቦቻችን ሰራዊቱን ማድረስና አጠቃላይ አስፈላጊ ስንቅና ትጥቅ ማቅረብ ነበር። በሁለቱም መጽሃፎች ስህተት የምላቸውንና ተጨማሪ አስተያቶችን ከማስታወሻዎቼ አቀርባለሁ። ከዚያ በፊት ግን፡- ወሳኝና የባሕር ሃይላችን አባሎች በምጽዋ የባሕር ሃይል መደብ የተሳተፍንበትን እልህ አስጨራሽ የምድር ከባድ የጦርነት ውሎ በማስቀደም ያለፍንባቸውንና መሆን ነበረበት የሚለውን የሚሰማኝንና ከአገለገልኩባቸው የጦር መርከቦች በወቅቱ ቅርብ ሃላፊ ለነበሩት ሁሉ በነበረኝ የኃላፊነት ቦታ በጣም ወሳኝና አንገብጋቢ የነበሩትን ሃሳብና ከተዋጊ ከባሕር ሃይላችን አባሎች ጋር እንደአቅማችን ካደረግነው ጥረትና ተጋድሎ ያደረግንበትን ከማስታውሳቸው ጥቂቶቹን እነሆ!

እንደወትሮው ሁሉ የሻቢያ የደፈጣ ወንበዴዎች በተደጋጋሚ የኢትዮጵያ ባሕር ሃይል ምጽዋ መደብንና በአካባቢው ያሉትን የነዳጅ ማከማቻና የወደብ እርዳታ ማከማቻና የልማት ቦታዎችን በረጅም የሮኬት ተወንጫፊ ሮኬቶች በመደብደብ የዘወትር ውንብድናቸው ነበር። በተለይም የምጽዋ ባሕር ኃይል መደብ ዋናው ኢላማቸው ነበር፡ የአካባቢውን የምድር ጦር አልፎም ይሁን፡ በምን ምክንያት ባልታወቀ ጉዳይ የምጽዋ ባሕር ኃይል መደብ የባሕር ጠረፍ ነበርና። የሚተኮስባቸውን ቀጠናዎች በተሰጡን የካርታ ምልክቶች ከምድር ጦሩ የምሽግም ይሁን ሰፈራ የጥበቃ ቦታዎች በነበሩን የመርከቦች ረጅም ርቀት ተወንጫፊ ሮኬቶች ለመምታት አስቸጋሪ ስላልነበሩ ፈጣን ምላሽ ለመስጠት COMMUNICATION ችግርና አካባቢውን ሙሉ በሙሉ በወታደራዊ ኃላፊነት የሚመራ ተሰሚነት ያለው( በጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥነትም ይሁን በመከላከያ ሰራዊት አዛዥ) ጥምር አስተባባሪ ባለመኖሩ ነው። ምክንያቱም፡ ክቡር ኮሞዶር ጌታቸው ስዩም የ NORTHERN NAVAL COMMAND አዛዥ በነበሩበት ጊዜ በአካባቢው ሲንየር ስለነበሩና የ6ኛ ክፍለጦር አዛዥ የነበሩት ኮሎኔል ሰለሞን( በኋልም ብ/ጄኔራልና የሓረር አካዳሚ ምሩቅና በመፈንቅለ መንግስቱ ተሳትፈዋል በማለት ከ6ኛ ክፍለጦር ወደ102ኛ አየር ወለድ ከተዛወሩ በኋላ በሚመሩት ወታደሮች የተገደሉት) ጋር በመቀራረብና የነበረውን የተጣመረ መግባባት በማወቀር በየጊዜው የጥምር ወታደራዊ ልምምድ ሲደረግ እንደነበር የሚታወስ ነው። ይህም ሆኖ ሳለ፡ የሻቢያ ዋናው ዒላማ የባሕር ኃይል መደብና የአጂፕ የነዳጅ ማከማቻ ጋን ለማፈንዳት በተለያዩ ጊዜያት በደፈጣ በረጅም ርቀት ሮኬት ተወንጫፊ ይሞክሩም የተሳካላቸውም ጊዜ ነበር። በባሕር ኃይል መደብ ውስጥም የክፍለሃገሩ የነዳጅ ማከማቻ ስለነበር ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ በደፈጣ ረጅም ርቀት መምታት የሚችለውን ግራድ ፒ በሚባለው ሮኬት ሞካክረዋል አልተሳካላቸውም። ሻቢያ ከሞከረባቸው አንዱ፡- ቀኑን የማላስታውሰው በ1979 እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር እለት እኩለ ሌሊት ላይ ከመደባችን በስተሰሜን በጉርጉሱም አቅጣጫ ለአርባ ደቂቃ ያህል ሲተኮስ ኢላማቸው በነበርኩበት የፈጣን አጥቂ ጦር መርከብ 111ኛ ስኳድሮንና ወደመደቡ PARADEGROUND አካባቢና ነዳጅ ጋኑ ላይ ነበር። በአንድ ወገን ላይ ብቻ ከባድ የመቁሰል አደጋ እንጂ ያንን ያህል የወነጨፉት የሮኬት ውርጅብኝ ሲካሄድ ከምድር ጦር ምንም ዓይነት የመልስ ተኩስ ባለመካሄዱ በባህር ቅኝት ላይ ለነበረችው FTB-11o የጦር መርከብ ትእዛዝ ተሰጥቶ ወደሚተኮስበት አቅጣጫ የእሩምታ ተኩስ ከባሕር ወደመሬት ሲካሄድባቸው ፈርጥጠው አምልጠዋል። እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲከሰት በአካባቢው ያሉት የምድር ጦር አባላት የሚተኮስበትን አቅጣጫ ለይተው ወዲያውኑ ምላሽ ስለማይሰጡ በባህር ላይ Patrol የሚያደርጉት የጦር መርከቦቻችን በረጅም ርቀት ሮኬት መምታት እየቻሉ፡ በዚህ ቦታ ላይ ይታየኛልና መምታቴ ነው ሲባል ከምድር ጦሩ የኛ ሰራዊት አለ የሚባልም መልስ ስለነበር ኢላማን መርጦ ለመምታት አስቸጋሪ ሁኔታዎችም ነበሩ። በዚህ ምክንያት ከምጽዋ ባሕር ኃይል መደብ ከፍተኛ መኮንኖች በቀረበው ሃሳብ መሰረት መደቡን ለመከላከልና ፈጣን ተኩስ አድርጎ የጠላትን ኢላማ በቀላሉ ለመምታት እንዲያስችል BM-21 40 ያኽል ሮኬት ጭኖ እስከ 25 ኪሜ መምታት የሚችለውን ኡራል በሚባለው መኪና ላይ የተጠመደ ተወንጫፊ፡ በኃላፊነት አተኳኮሱንና እንዴት OPRATE እንደሚደረግ የሚያስተምሩ አባላት ከምድር ጦር ተመድበው በመደቡ GUNNERY WORKSHOP ከምንሰራው ሶስት አባላት ተመርጠን ለሁለት አባላት እንድንማረው ከመደቡ አዛዥ ከካፒቴን ኃይለሚካል ከበደ ትእዛዝ እንደተሰጠን፡ እኛ የተማርነው NAVAL GUNMOUNTS, TORPEDO, MISSILE መሆኑን እያወቁ ካፒቴን እባክዎ የማሪን ኮማንዶ አባላት ቢማሩትና ቢረከቡ የተሻለ ነው፡ የእግረኛ ሰራዊቱም ጋር በሚገባ ሊያደርጉት የሚችሉት እነርሱ ናቸው ብለን ሃሳብ ስናቀርብና ከእርሳቸው ጋር ለ2 ዓመታት በፈጣን አጥቂ ጦር መርከብ FMB -160 ሳገለገል በ AK-230 mm መድፍ SIGHT COLUMMNIST OPRATOR ስለነበርኩና የመርከባችንም ካፒቴን ስለነበሩ፡ እናንተ ልምድም ስላላችሁ በቀላሉ ትለምዱታላችሁና በአስቸኳይ ትምህርቱን ቀጥሉ የሚል ምላሽና ቀጥተኛ ትእዛዝ ሲሰጡን ትእዛዙን ተቀብለን ለሁለት ቀናት ተማርነው እንዳሉትም አስቸጋሪ አልነበረም። እናም ከመርከብ መድፎች ጋር ስናስተያየው ያው የመርከብ መድፍ በውሃ መርከብ ላይ ተንሳፋፊና ኢላማ ለመምታት ሰፋ ያለ ልምድ ይጠይቃል፡ ከመርከብ መድፎች ጋር ስናስተያየው ቀለል ያለ ቢሆንም፡ አንዱን የሮኬት ጥይት እንኳን በቀላሉ ለማጉረስ ከባድ በመሆኑ በጦርነት ጊዜ የሰው ኃይል እንደሚመደብ ተነግሮን ከሁለት ቀን በኋላ በአካባቢው ያለውን በ20 ኪሜ ያለውን ክልል ካርታ አዘጋጅተንና CALCULATE በማድረግ ተኩሱን

ተለማምደን በ GUNNERY WORKSHOP በራፍ ላይ ሙሉውን 40 እንደጎረሰ ለድንገተኛ ጦርነት ፈጣን ተኩስ ምላሽ አዘጋጀነው።

ጥር 30 ቀን 1982 ምሽት ላይ የከባድ መሳሪያ ተኩስና ፍንዳታ ከምጽዋ ባሕር ኃይል መደብ በስተሰሜን ሲተኮስና ከጠላት የተተኮሰው ሲወድቅ ከርቀት ቢሆንም ተደጋጋሚና የማያቋርጥ በመሆኑ፥ በባሕር ኃይል መደብ በተለያዩ WORKSHOP የምንሰራው አባላት፥ ምንድነው ነገሩ? ብለን አናዳንድ ከፍተኛ መኮንኖችን ስንጠይቅ ልምምድ ነው መሰለን የሚል ምላሽ ነበር የሚሰጡንና ሁላችንም ግራ የመጋባት ሁኔታ ውስጥ ነበር ያለነው። ይኽም ሆኖ ሌሊቱን ተኩሱ መሬቱንና ሕንጻዎችን ሲነቀንቅ ከጠላት የሚተኮሰው ሲወድቅ እንደሆን ጠረጠርንና በመደቡ ውስጥ ብቻ በሚሰሩት የውስጥ መስመር ስልኮች እየደወልን ይመለከታቸዋል ብለን የምንቀርባቸውን ብንጠይቅ ሁኔታውን እንደማያውቁ ሲነግሩን ያለምንም እንቅልፍና እረፍት አደርን።
ጥዋት የካቲት 1 ቀን 1982 እንደተለመደው በመደቡም ይሁን በወደብ ያሉት የጦር መርከቦች ላይ የሚሰሩት አባሎች እንደወትሮው ሁሉ ስራቸውን ቀጥለዋል። የተኩሱ ኃይል ከመቅረቡም ባሻገር ለጦርነት ተዘጋጁ የሚለው ALARM ሳይነፋ ወደየውጊያ ምድብ በራሳችን ጊዜ ለመሰናዳትም በተጠንቀቅ መሆን እንዳለብን እርስ በራሳችን መነጋገር ጀምረናል፥አሳሳቢና ያልተለመደ ነገር ሆኖብናል፥ እንኳንስ ተኩስ ቀርቦና፥ አደጋ እንደሚጣልብን መረጃ እንኳን ሲኖር FIRST DEGREE READINESS ተብሎ ለመላው የጦር መርከብና መደብ ሰራዊት ይነገርና ሁሉም በተጠንቀቅ ይዘጋጅና ለግዳጅ ብቁ ነበር። ከመላው የባሕር ኃይል መደብ አባላት የመጡ ሲሆን፥ የእጩ መኮንኖች ምረቃ በዓልና የባሕር ኃይላችን የተመሰረተበትን 34ኛ ዓመት በዓል በወቅቱ ዝግጅት ነበር።

በPARADEGROUND የሰልፍ ልምምድ በ1982 ምልምል መርከበኞች በስፖርት ልብስና በመደበኛ የባሕር ኃይል ዩኒፎርም የሰልፍ ልምምድ እየተደረገ ሳለ፥ የመጀመሪያው የግራድፒ ሮኬት ጥይት እራሴ በምሰራበት የ GUNNERY WORKSHOP ጀርባ ባሕር ላይ ወደቀ። ወዲያውኑ ከባሕር ኃይል መደብ የክተት አዋጅ(ALARM) ተነፋ(ታወጀ)።
ሁሉም የምጽዋ ባሕር ኃይል መደብ አባሎች በየውጊያ ቀጠናቸው ተሰማሩ።፥በወደብ የነበሩትም የጦር መርከቦች ወደ ባሕር ተሰማሩ።
ወዲያውኑ የ BM-21 ሮኬት ወንጫፊ ለምንተኩሰው መድፈኛ ሶስት አባላት፥ የ 4 OBSERVER POSITION(አስተኳሽ) የሬድዮ ኮድ ተሰጥቶን መነጋገር እንደጀመርን ከመደቡ በስተሰሜን ወደጉርጉሱም አቅጣጫ ወደግራ ሁለት ኪሜ ከመደቡ 16 ኪሜ እንድንመታ ዒላማ ተሰጠን። ቀድሞውንም በታላቅ ሞራል ተዘጋጅተንበትና እንዲያውም ከባሕር ኃይል መደብ ግቢ ወጥተን እግረኛውን እርዱ የሚል ትእዛዝ እነጠብቅ ነበርና በአስቸኳይ በካርታችን ካለው መረጃ በመለካት የተባለውን ቦታ LEADING SEAMAN QUARTER ከሚባለው አመቺ ቦታ በመሆን የመጀመሪያውን ፍጥነታዊ አውቶማቲክ ተኩስ ጀመርን። ከአስተኳሻችን ፈጣን ምላሹ አንበሳዬ እንዲህ ነው እንግዲህ ባሁኑ አቅጣጫ 5 ኪሜ ላይ ድገምልኝ የሚል ኢላማ ሰጠን። ልክ ተኩሱን እንዳደረግን በቅርብ ርቀት ወደኛ የሚተኩስ የጠላት አጭር የሮኬት ሊኖር ይችላል ብለን ገምተን ስለነበር፥ በወቅቱ አነስተኛ የባሕር ክፉይ ላይ ካለው ከሲሚንቶ ፋብሪካው የ1.5ኪሜ ላይ የሻቢያ ሞርታር ተኳሾች ተኩስ አዘነቡብን። አቅጣጫው ወደኛ ቢሆንም በርቀት ሄዶ በማረፉ፥ ፈጣን በሆነ ሁኔታ 40 ያህል ሮኬቶችን መጫን የሚችለው ኡራል መኪና ቦታውን በመቀየር የታዘዝነውን ዒላማ ከ OUT DOOR SINEMA ጀርባ ሆነን ለቀቅንበት። አስተኳሻችን ይኸው ነው አንበሳዬ የሚል ምላሽ እንደሰጠን ከዶጋሊ ወደምጽዋ መስመር ፎርቶ ላይ እንድንመታ ሌላው አስተኳሻችን እንድንፈጥን ነገረን። ወዲያውኑ በሶስት ሮኬቶች የተባልነው ቦታ እንደተኮስን ካሁኑ ኢላማ የ 500 ሜትር ጭማሪ አድርጉ እንዳለን፥ በተባልነው መሰረት ፍጥነታዊ ተኩስ እንዳደርግን አንበሳዬ ልክ ነው ልክ ነው፥ እንዳለን ለሌላ ተኩስ ከአስተኳሾች ስንጠባበቅ፥ ከምጽዋ ባሕር ኃይል መደብ ዘመቻ መምሪያ አመቺ ቦታ ይዛችሁ በጉርጉሱም አቅጣጫ ታንኮችና እግረኛ ሰራዊት ይታያሉና ወደኢላማ ተባልን፥  በነበረን የጦር ሜዳ መነጽር ስንመለከት የጠላት ታንኮች ረድፍ ሰልፍ ተመለከትን። ስውር ተኩስ ቀረና ፊት ለፊት ውጊያ(DIRECT FIRE) ሆነ ነገሩ ሁሉ። የጀግናው አየር ኃይላችን አብራሪዎች የጠላት ታንኮችንና ከባድ መሳሪያዎ ኢላማዎችን ሲያጠቁ ካለንበት ሆነን ስናይና ለሌላ ተኩስ ስንዘጋጅ ችሎታቸው እንዲህ ነው ብሎ ለመናገር ቃላቶች ያጥሩኛል። ድብደባውን ለማድረግ ከባሕር ወደመሬት ተዋጊ አይሮፕላኖችን ፓይለቶቻችን እየተወረወሩ ሲያጠቁ፥ የኛ ተወንጫፊ እንዳያገኛቸው ስንል ለጥቂት ደቂቃዎች ጠበቅንና አቅጣጫቸውን አይሮፕላኖቹ እንደለወጡ የተባልነውን ኢላማ ውስጥ እንደገባልን አውቶማቲክ ተኩስ አደረግን። ወዲያውኑ በፈጣን አነዳድ መኪናውን የሚነዳው ብሔራዊ ወታደር በማንቀሳቀስ በአስተዳደር ሕንጻ ፊት ለፊት ስናልፍ ከሕንጻው ፎቅ ላይ ሆነው የኢላማውን ድብደባ በጦር ሜዳ መነጽር ሲመለከቱ የነበሩት ካፒቴን ኃይለሚካኤል ከበደና አብረዋቸው የነበሩት ከፍተኛ መኮንኖች፥ በአውራ ጣቶቻቸው ምልክት በማሳየት በርቱ ሲሉን ሮኬት ወደሚጫንበት አቅጣጫ አመራን።
ከሻቢያ ወደ ተዋጊ አይሮፕላኖች የሚተኮሰው አየር መቃወሚያ ጥይት በከፍታ ተተኩሶ በአየር ላይ ሲፈነዳዳ

ፓይለቶቻችን የሚተኮስባቸውን በመቋቋምና አይሮፕላኖቻቸውን አቅጣጫ በመለዋወጥ ያደረጉት ተጋድሎ አስደናቂና ካየር ተወርውረው የሻቢያን ታንኮች ሲያቃጥሉ ማየት ለኛም ታላቅ የውጊያ ሞራል ነበር።

የምጽዋ ባሕር ኃይል መደብ ከጀርባው ባሕር እንጂ ለምድር ውጊያ የሚያመች ገዢ መሬት የሌለው ቦታ ነውና ማድረግ ያለብንን ሁሉ ለማድረግ በቆራጥነት እያደረግን ሳለ፡ የBM-21 ወንጫፊ ወደሚቀጥለው ግዳጅ ኢላማን በማስተካከል ሮኬቶችን በጠላት ብረት ለበሶቹ ላይ አወረድንባቸው። ይህ ሁሉ ሲሆን የኛን አቅጣጫ እየተከተሉ የሚተኩሱ ሞርታሮች በፍጹም ሊያገኙን አልቻሉም። በተለይም በስፖርት ሜዳው ላይ ሆነን ስንተኩስ 3 የሚሆን የሞርታር ፍንዳታ በአቅጣጫችን ትይዩ ተተኩሶ ሊያገኘን አልቻለም። ከኋላችን አልፎ በባዶ ሜዳ ላይ ፈነዳ። የሻቢያ ከባድ መድፎችና ግራድፒ ሮኬቶች በግቢው ውስጥ ያለማቋረጥ እየወደቀ ሕንጻዎችን ቢያፈራርስም አብዛኛው ወደባሕር ሲወድቅ ነው የሚታየው። የተኮሱት ሁሉ በግቢው ውስጥ ቢያርፍ የሚተርፍም አይኖርም ሕንጻ ከማፈራረስ በስተቀር።

ከፎሮ ተወርውሮ ለእርዳታ የመጣው በታላቅ ጀግንነት የሚዋጋው በኮሎኔል በላይ አስጨናቂ የሚመራው የጀግናው 27ኛ ሜካናይዝድ ሰራዊት ባሉት ታንኮቹና የ6ኛ ክፍለጦር ጀግና ተዋጊዎች፡ ምጽዋ ጥዋለት ላይ አመቺ ቦታን በመያዝ ታላቅ የጀግነት ተጋድሎ ማድረግ ጀምረዋል። እንዲሁም ሶስተኛ ሜካናይዝድ የቀሩትን ታንኮች ይዞ በማፈግፈግ በምጽዋ ባሕር ኃይል መደብ ግቢ ሆኖ በመከላከል የሚቻላቸውን ሁሉ ከመደቡ የባሕር ኃይል ሰራዊት ጋር ያለምንም እረፍት ታላቅ ተጋድሎ ሲያደርጉና ከከፍተኛ መኮንኖች እስከብሔራዊ ወታደር የነፍስ ወከፍ መሳሪያቸውን ታጥቀው በተጠንቀቅ መጠባበቅ ላይ ሳሉ፡ ክቡር ኮሞዶር በለገ በለጠና አንበሳው ክቡር ኮሞዶር ጌታቸው ስዩም የተናገሩት ቃል(አንበሳው ያልኩት የማሪን ኮማንዶ አባላት የሰጧቸው ቅጽል ስም ነው) በግቢው ውስጥ በመከላከል ላይ ላለው ሰራዊት፡ “ የሃገራችንን የባሕር በር በመጠበቅና በመከላከል ከወጣትነት እስከ ጎልማሳነት የባሕር ድንበራችንን ስናስከብር መነሻችንና የባህር ኃይል መዲናችን የምጽዋ ባሕር ኃይል መደብን ተዋግተን እስከመጨረሻው እንታገላለን እንዋጋለን ሁሉም አባል እግረኛው ወደሚዋጋበት ዋናው የመደቡ ዋና በር መከለከል እንዲያደርግ መዘጋጀት አለበት “፡ ብለው በአካባቢያቸው ላሉት ከፍተኛ መኮንኖች ሃሳብ እያቀረቡ ሳለ፡ መሳሪያችንን ሮኬት እያጎረስን ሳለ፡ የአካባቢው የ ኮ/ር አዛዥ ብርጋዲየር ጄኔራል ጥላሁን ክፍሌ በቀጥታ ወደምጽዋ ባህር ኃይል ኦፕሬሽን መምሪያ ሲያመሩ ተመለከትን። የ6ኛ ክፍለጦር አዛዥ ክቡር ብርጋዲየር ጄኔራል ተሾመ ተሰማም በዚሁ በመደቡ ግቢ ውስጥ እንደገቡ በባሕር ሃይል ባሕር ጠለቅ ኮማንዶ ZODIAC ጀልባ ምጽዋ-ጥዋለት ላይ አፈግፍጎ ያለውን ጦር እንዲመሩ ወደ ርእሰ ምድር ተሻገሩ።

BM21 ላይ ለነበርነው አባላት አስቸኳይ ድብደባ እንድናደርግ በፎርቶና ከፎርቶ ወደቀኝ ባሉት ቦታዎች ላይ የሚል ትእዛዝ ነበር። ድብደባውን ያደርግነው፡ DIVING SECTION አጠገብ ሆነን ስለነበር ቦታውን በግልጽ የምናየው ከመሆኑም በላይ በአካባቢው የነበሩት የምድር ጦር አስተኳሾቻችን ምላሽ አንበሳዬ ትክክል ነው ልክ ነው የሚል ምላሽና አድናቆትን ያዘለ የሞራል ዜማዊ ድምጽ ነበር። ይጎንን ሮኬት ወንጫፊ መሳሪያ አጠቃቀማችን ለየት ያደረገው ለአንድ አካባቢ ኢላማ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ካርታችንን እየለካን በፍጥነት መኪናውን ከቦታው ወደሚቀጥለው እንቀይራለን። ከመደቡ ኦፕሬሽን ጀርባ በብሔራዊ ወታደሮችና እጩ መኮንኖች ረዳትነት ጥይት አጉርሰን ወደተለያዩ ቦታዎች ስናመራ በድንገት ጄኔራል ጥላሁን ከባህር ኃይል ዘመቻ መምሪያ ፊት ለፊት ባለው አጥር ስር አስቆሙንና ስትተኩሱ አቧራ የማይነሳበት ቦታ ሆናችሁ ተኩሱ የሚል ትእዛዝ ሲሰጡን ሶስታችንም ተያይተን ተገርመን ሳለ የአስተኳሾቻችንም ድምጽ ከሬድዮ በመጥፋቱ በቀጥታ ወደሚመቸን ቦታ አመራን። ሮኬቱ ሲተኮስ ከ25 ሜትር በላይ ወደኋላ የሚወረወር የእሳት ወላፈን አለው። የመደቡ ግቢያችን ደግሞ አነስተኛ ከመሆኑም በላይ የምንመርጠው ቦታ የለንም። ያመቸን ቦታ ሆነን የጠላትን ኢላማ መምታትና የሚቻለንን ማድረግ ብቻ ነበር ግዳጃችን። የምናንቀሳቅሰው ከባድ መሳሪያ፡ የምድር ጦር ለእግረኛ ሰራዊቱ ከበስተኋላ ከርቀት ሆኖ የተኩስ ድጋፍ የሚሰጥበት ሆኖ ሳለ፡ በወቅቱ ግን ከጠላት ኢላማ ጋር ቅርብ ብንሆንም ለቀጥታ ተኩስ ከወንጫፊው ቧንቧ(BARREL) ቁጥር 27 ላይ መስቀለኛ ማነጣጠሪያ በማድረግ፡ ማድረግ የምንችለውን ሁሉ እያደረግን ከተኮስን በኋላ በፍጥነት ቦታን መቀየር ልክ እንደጦር መርከቦች MANUVERING ዓይነት እንቅስቃሴ ነበር። ከርቀት በርግጥ የሻቢያ ከባድ መሳሪያዎችና ታንኮች ዋና ኢላማ ያደርጉት የኛን BM ስለነበር ቦታችንን እንደቀየርን ወደሚነሳው አቧራ ሲተኩሱ በትናንሽ ምሽጎች ውስጥ ባሉት የኛ ወታደሮች ላይ የጠላት መድፍ ጥይት እንዳያርፍ፡ በአካባቢው ያሉትን ቦታ ቀይሩ እያልን እንናገር ነበር። የፈሪ ዱላና ያላሰቡት ያልጠበቁት ሆኖላቸው አፈግፍጎ ወደ ባህር ኃይል ግቢ የተሰባሰበላቸውን ተዝናንተው እንደሚተኩሱ የነበረው INTERVAL ጊዜ ያስታውቅ ነበር። ቀኑን እንዲሁ ውለን፡ ከለሊቱ (ስምንት ሰአት ላይ) 0200 GMT ላይ የሻቢያ ፈጣን ጀልባዎች አደጋ ለማድረስ ወደ ጦር መርከብ ኢትዮጵያ ሲያመሩ በ40 ሚሜ መድፍ የቀረቡትን ሁሉ እንደጧፍ ስታነዳቸው ከመደቡ ሆኖ ይታይ ነበር።

ለመላው በመደቡ ውስጥ ላለ ወታደር ማለትም አፈግፍጎ ወደመደቡ የመጣው የ6ኛ ነበልባል ክፍለጦርና የ3ኛ ሜካናይዝድ ወታደሮች ባሉት ታንኮቻቸው፡ ከኮሞዶር በለገና ኮሞዶር ጌታቸው ስዩም ጥብቅና ወሳኝ ትእዛዝ መጣ፡ ከወጣትነት እድሜያችን አንስቶ እናት ዓለም ኢትዮጵያ የባሕር በሯን ለማስከበር የባሕር ኃይላችን

የተመሰረተባትን የባሕር ኃይል መዲናችንን እናስከብር፡ በነፍስ ወከፍ መሳሪያ ሁሉም አባል ከከፍተኛ መኮንን ጀምሮ ወደፊት!!!! ተባለ። በመኪናው ላይ ጎርሶ የቀረን 17 ያህል የሮኬት ጥይት ብቻ ነበር። መኪናውን FSS STORE አጠገብ የባሕር ዳርቻ ከኋላችን ትተን፡ በትእዛዙ መሰረት ወደጎን በረድፍ በመሰለፍ ከክቡር ኮሞዶር በለገ በለጠ በነበረው ረድፍ ጋር ነበር፡ አጋጣሚ ሆኖ የተሰለፍኩት።

የሻቢያ እግረኛ ጦር እስከእዳጋ ሰፈር ደርሷል። (ከምጽዋ ባሕር ኃይል ዋናው በር የ300 ሜትር ርቀት ቢኖረው ነው ግራር ሰፈር) ሁሉም በመደቡ ግቢ ውስጥ ያለ ወደዋናው በር ተንቀሳቅሶ ዋናው በር ላይ እየተከላከሉ ካሉት የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል ማሪን ኮማንዶዎችና የምድር ጦር አባላት ጋር ተቀላቀልን። IFA በሚባለው የምድር ጦራችን መኪና ላይ የከባድ መድፍ ጥይት እንደተጫነ አፈግፍጎ ዋናው በራችን ላይ ሳለ ግራር አካባቢ የነበር መድፍ ተኳሽ የጥይት ያለህ አቅርቡልኝ፡በማለት አጠገቡ በነበረው ሬድዮማን ሲናገር፤ እስቲ ደፋር ሾፌር ሲባል፡ እኔ በፈቃደኝነት እነዳለሁ ብሎ የባሕር ኃይል ባልደረባው ማእረጉን አላስታውስም ደበበ ቱኬ ይባላል። መኪናውን አንቀሳቅሶ ሲጓዝ ግራር አካባቢ እንደደረሰ ከርቀት በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ ከነመኪናው በመመታት ተሰውቷል። ይህ ወጣት ከማይረሱኝ ውድ የባህር ኃይላችን ኢትዮጵያዊ ጀግና ነበር። ለነበረው መድፍና  ሻቢያ በመድፍ እየተረዳ በአካባቢያችን ላይ ቢያወርድም ኢላማቸው ከምጽዋ ሆስፒታል ጀርባ ምዕራብ ቀጣና ኮንክሪት ምሽግ ላይ ነበርና ምሽጉ እንዳለ ሲፈራርስ የጠላት እግረኛ ግራር ላይ በመድረሱ የተረፉት ከኛ ጋር ተቀላቀሉና ከግራር እስከመደቡ ዋናው በርና አጥሩ ስር በመመሸግ በነፍስ ወከፍ መሳሪያ ውጊያው ተጋጋለ። በአካባቢያችን ዋናው በር ላይ የተሰዉት ክቡር ኮማንደር አስቻለው ጀማነህ፡ ፒኦ ክብሮም(ማሪን ኮማንዶ) ፒኦ ዝናው አረጋ ነበሩ።

የምድር ጦር አባላት ማሪኖችና ከዋናው በር ወጣ ብሎ ባለው የምጽዋ ሆስፒታል በር አካባቢ ወደግራር ሲታኮሱ የተሰዉት ክቡር ኮማንደር ኃይሉ አጠገባቸው የነበረው ተርፎ ወደኛ የተቀላቀለው MY INTAKE ፒ/ኦ ሰለሞን ተፈራ(ኩባ) እጁ ላይ ክፉኛ ቆስሎ ነበር(አሁንም በሕይወት ያለ)። በግቢው ውስጥ ከግንባር አፈግፍገው የመጡት ታንከኞች ባሉት ታንኮች ኢላማ እየመረጡና የወገን ነው እናውቀዋለን ያሉት የጠላት ታንክ ቀለሙም ከኛዎቹ ታንኮች ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ እንደገባ ከላይ በተጠመደው ማሺንገን ተኩስ ሲከፍት፡ ከወገን ተተኩሶበት በማምለጥ ላይ ሳለ በግራር ትይዩ ቦታ ላይ ከጥቅም ውጪ ሆኗል። በዋናው በር ትንቅንቅ የማይረሳኝ በፉከራና በሞራል የሚታኮሱ የባሕር ኃይላችን አባላትም ነበሩ። ምድር ቀውጢ ሆነች፡ በመደቡ በር አጠገብ ያለው ሕንጻ ከጠላት ታንክ በተኮሰ ጥይት ሲመታ ፍርስራሹ የጎዳቸውና ክፉኛ ያቆሰላቸውም ወገኖች ነበሩ። ወደ እዳጋና የጨው ማሳው ላይ ወደ ፊት ለፊታችን የጦር መርከቦቻችን ከባሕር የሚያዘንቡት የመድፍና የሮኬት ተወንጫፊ ከምጽዋ ሆስፒታል ጀርባና ከፊታችን ባለው የጨው ማሳ ላይ የሚርመሰመሰውን የሻቢያ እግረኛና ታንከኛ ድንግርግሩ እንዲወጣና ፈጣን የነበረውን የሻቢያ ማጥቃት ለጊዜውም ቢሆን ገቶት ነበር።  ጠላት ሰአቱም እየመሻሸና ሻቢያም በማያቋርጠው የመድፍ ድብደባ ለማዳከም የሚያወርደውን ለረጅም ዓመታት በጦር ግምባር የረጅም ጊዜ ልምድ ያላቸው የምድር ጦር አባላት፡ እንደዚህ ዓይነት ውጊያ በሕይወታችን አይተን አናውቅም ነበር የሚሉት። ሻቢያም በቀላሉ የምጽዋ ባሕር ኃይልን መደብ በቀላሉ ሊይዝ ይቅርና መሸት እንዳለ ተኩሱን አቆመ። ከምጽዋ ሆስፒታል ጀርባ ወይም ከምእራብ ቀጣና ጀርባ በሻቢያ ሰራዊት ስር ወድቋል። የረጅም ርቀት መድፍና ሮኬት ወንጫፊ መሳሪያ ያላቸው የጦር መርከቦቻችን፡ ጦር መርከብ ኢትዮጵያ፤ ጦር መርከብ 1037 LANDING CRAFT, LANDING CRAFT-1038, FRIGATE- 1616 እና ሌሎችም ሆነው፡ ከባሕር ሆነው ከኛ ፊት በነበረው የጠላት ታንክና እግረኛ ሰራዊት ላይ ያደረጉት ድብደባ አስተዋጽኦው በጣም ከፍተኛ ነበር። ለዚህም ነበር ከግራር ወደ ባህር ኃይል ግቢ ለማጥቃት ያልቻሉት፡፡  ዋናው በር ላይ አስተማማኝ ምሽግ ባይኖርም የተደረገው መከላከል ከተጠበቀው በላይ የተጋድሎ ሁኔታ ነበርና ወደኋላ በማፈግፈግ ከባሕር ኃይል ፖሊስ ሕንጻ ጀርባና ለጊዜው አመቺ ነው በሚባለው ሁሉ ነገር አድፍጠን መከላከልና የቆሰሉ አባላትን ሓኪሞች ማግለል ጀምረው ነበር። በዚያን ወሳኝ የመጨረሻው የዋናው በር ርብርብ ሰአታት እነማን እንደተሰዉ ለማወቅና ለማስታወስ አስቸጋሪ ነው።  በሆስፒታሉ ግቢና በባሕር ኃይል ፖሊስ ሕንጻ መካከል ገላጣ ሜዳ ወይም ሰፉ ያለ ክፍተት ስላለ የጠላት እግረኛ ለማጥቃት ከሞከረ፡ በዚያች ሰአት እንደሚያልቁ ስለገመቱ ለጥቂት ሰአታት የመድፍ ድብደባ ብቻ በማድረግ ተወሰኑና ተኩስ አቆሙ።
የሻቢያ ኃይል ሲበረታ የተረፍነው ወደኋላ ማፈግፈግ ግድ እንደሆን ኮሞዶር በለገ እነደተናገሩና በ1036 ምድረነክ የጦር መርከብ ስፓርታኪያድ በሚል የሚጠራው እግረኛ የወገን ጦር ምሽት ላይ እንደወረዱ፡ ያለምንም እረፍት ቦታ ቦታ እንዲይዙና እንዲዘጋጁ የመሬቱን አቀማመጥ በጭለማ እያሳዩዋቸው ሳለ፡ ኃይለኛ የከባድ መሳሪያና የነፍስ ወከፍ መሳሪያ ውጊያ ተጀመረ። በግምት ለሰላሳ ደቂቃ ያህል የተኩስ ልውውጥ ከተካሄደ በኋላ፡ እንደገና ጠላት ተኩሱን አቁሞ ጸጥ አለ።
ውሃም ሆነ እህል ከቀመስን ሁለት ቀናት አልፈውን ስለነበርና፡ እንደምድር ጦር ደረቅ ራሽን የሚባልም ነገር ሆነ ውሃም ስለሌለን በአካባቢው ለአትክልት ተብሎ በዛገ በርሜል የተሞላ ውሃ አግኝተን ባገኘነው ነገር በመጠጣት ተንፈስ ብለን ሞራላችን አድሰን፡ አብረን የነበርነው ጓዶች፡ ሌሊቱን MARRIED QUARTER በሚባለው ቦታ ሆነን ጥይት የሌለው ካለውና ከተሰዉ ወገኖች መሳሪያዎችንና ጥይት ከያለበት ሞላልተን ተራ

በተራ የዶሮ እንቅልፍ ዓይነት በማንቀላፋት በታላቅ ሞራል ለወሳኙ ፍልሚያ ተዘጋጀን።

የካቲት 2 እና 3 1982 ዓም፡ በተለያዩ ሰዓታት ከሻቢያ ተኩስ የቆመ ቢሆንም፡ የጦር መርከቦቻችን ከባሕር በሚወነጭፏቸው ሮኬቶችና ከባድ መድፎች የሻቢያን የከባድ መድፍ አካባቢ ሲያራውጡ ከመደቡ ይታይ ነበር። ሌፍትናንት መኩሪያ ዲዲማና ጁኒየር የሸዋለም ነጋሽ፡ ያደርጉ የነበረው የውጊያ ማስተባበር ተጋድሎ ምን ጊዜም አይረሳኝም። በተለይም ሌፍትናንት መኩሪያ ዲዲማ በግራ እጃቸው ዱላ በቀኝ እጃቸው ታጣፊ ክላሽንኮቭ ጠመንጃ ይዘው የሚሸሸውን ከየስርቻው በማውጣት በረድፍ እንዲሰለፍና ከምጽዋ ባሕር ኃይል መደብ ሲኒማ ቤት ጀምሮ በረድፍ አሰላለፍ ወደዋናው በር የእግረኛ ማጥቃት እንዲደረግ አዘዙ። እርሳቸውን ሳውቃቸው በወታደራዊ ስነስርአት በጣም አክራሪና ስህተት የማያልፉ በእስራኤል የኮማንዶ አሰልጣኞች በ1958 ዓም የሰለጠኑ እንደነበሩ ታሪካቸውን የሰማሁ ሲሆን ወታደራዊ ደህንነት ተብሎ በኮሎኔል ተስፋዬ ወ/ስላሴ የሚታዘዘው አንዱ የመንግስት መሰለያና ማፈኛው ድርጅት ውስጥ በመሆናቸውና በሚያደርጉት አክራሪና ከወታደራዊ ሕግ ከሚፈቅደው በላይ በሚያሳዩት ባሕርይ ከሲቭል እስከባሕር ኃይል አባላት የምንጠላቸውና የምንሸሻቸው አባል ቢሆኑም ጀግና ተዋጊ ኢትዮጵያዊ ስለመሆናቸው ከተግባራቸው በውጊያው ላይ ያየናቸው እንመሰክራለን። ከተለያዩ ክፍል አፈግፍገው የመጡ የምድር ጦር አባላትና የምጽዋ ባሕር ኃይል በአንድነት ለመጨረሻው ፍልሚያ ወደፊት ሲባል፡ ከእኔ ጋር አንድ ላይ ለነበርነው አባላት በሌፍትናንት መኩሪያ ዲዲማ የተሰጠን አቅጣጫ ከኮሌጅ ባራክስ ወረድ ብሎ በተለምዶ ከሌሎቹ የመደቡ ቦታዎች ሞቃታማ ስለሆነ፡ሲናይ በሚል ቅጽል ስም ከሚጠራው አካባቢ ጀምሮ ወደዋናው በር በረድፍ ማጥቃት እንድናደርግ ተነገረን። ጎን ለጎን ከነበሩት ጓዶቼ የማስታውሳቸው:- ፒኦ ፍቃዱ አበራ(የቅርብ ጓደኛዬ)፤ ፒኦ ደሳለኝ አላና፤ፒኦ ቸሬ(1970 INTAKE) ሰብ ሌፍትናንት ዳኜ(RADIO MAN 1969 INTAKE) 1982 ምልምል መርከበኞችና ሁለት የምድር ጦር አባላት ሲሆኑ፡ በታዘዝነው መሠረት ወደፊት ስንነቃነቅ ከበስተግራችን ከባሕሩ ማዶ እስከ200 ሜትር ርቀት ቢሆን ነው ወደግራር ሰፈር መርከቦች ጨው ወደሚጭኑበት አቅጣጫ SCRAP ተደርገው ከጥቅም ውጭ ሆነው የተጣሉት የድሮዎቹ PATROL CRAFT መርከቦች ላይ በመሆን ጠላት ከግራ ጎናችን በእኛ ላይ በማሳለፍ ወደ SEAMAN MESS አቅጣጫ ያሉት ወገኖች ላይ ጥይት ሲያዘንቡ አቅጣጫው ተምታቶብን፡ በአጠገባችን ካለው የቀድሞ ምሽግ ውስጥ ገባን፡ ፒኦ ፍቃዱም፡ እኔም የያዝነው ከተሰዋ ወገን የወሰድነው RPG መትረየስ ስለነበር፡ ፒኦ ፍቃዱ እንዴት እንዳያቸው አላውቅም ተመልከቱ ፒሲዎቹ ላይ ሲለን በአንድ ላይ እንድንተኩስ ተጠቃቀስን፡ አንዳቸውንም አልሳትንም። ጠላት ከተጣሉት መርኮቦች ጀርባ ባሉት ቤት ላይ ተሸሽገው የሚተኩሱትን እነቸሬና ሰብሌፍትናንት ዳኜ ይለቅሙ ነበር።፡ሰብሌፍትናን ዳኜ ጭንቅላቱ ላይ የጨረፈው ጥይት ከመታው አንድ ቀን ተኩል ቢሆንም በታሰረለት ፋሻ ደሙ ቢቆምም ድካም ቢታይበትም፡የነበረው ሞራልና በአካባቢው ለነበርነው ሁሉ አበረታችነቱ ምንጊዜም ከፊቴ ትዝታው አይጠፋም፡ ታላቅ ጀግና ነበር።

የጠላት መድፍ ውርጅብኝ የኼን ያኽል ነበር ተብሎ ለመግለጽ አይቻልም፡ በቃ የፈሪ ዱላ። ያችን ለምታክል ግቢ ያለማቋረጥ እያወረዱ እነደተኮሱት ኢላማ ቢያገኙ፡ ያለምንም እግረኛ ውጊያ መቆጣጠር እንደሚችሉ ግልጽ ያለ ሁኔታ ነበር። ከዋናው በር ወደኛ አቅጣጫ የጠላት እንቅስቃሴ እነደተጀመረ፡ ከባሕር ላይ የቢኤም ሮኬት በ1037 ይሁን 1038 የጦር መርከብ ከሩቅ ትታየን ነበር፡ በላያችን አልፎ ከፊታችን አውቶማቲክ የሮኬት ፍንዳታ አካባቢውን ሲያናውጠው ወደኛ የተነቃነቁትን ዶጋመድ እንዳደረጋቸው ግልጽ ነበር። የተረፉት ወደኛ ሲነቃነቁ በሞራል ኢላማ እየመረጥን ማድረግ የሚገባንን እየተንከባለልንም እየተንፏቀቅንም ማከናወን ጀመርን በአጠገባችን ያሉትን የጠላት ሬሳዎች መታወቂያና መረጃ ይኖራል በሚል ስንፈትሽ ወረቀቶቹ የሕወሃት መሆኑን ያረጋገጥነው ቦታ ቀይረን እነደገና MARRIED QUARTER አካባቢ ከሆንን በኋላ ነበር። ቦታው ላይ ልንቆይ ቀርቶ ከፊታችን ከመርከቦችም ከጠላትም የመድፍ ፍንዳታ ወደፊት የማያስገፋና ከመርከቦችም ጋር ምንም ዓይነት የሬድዮ ግንኙነት አልነበረንም። መርከቦች የሚተኩሱት ከባሕር ሆነው የጠላት ኢላማ ነው ብለው ያመኑትን የሚታያቸውን ብቻ ነበርና። በተለይም 1037 ምድረነክ ጦር መርከብ በኛ አቅጣጫ የምትወረውረው ተወንጫፊ ታላቅ አስተዋጾ ነበረው። የጠላት እግረኛው ክፍል በአዲስ ጉልበት እየተቀያየረ እንደሚያጠቃን የያዘው ሰፊ ገዢ መሬት አመቺ ሁኔታን ፈጥሮለት ነበር። ይኽም ሆኖ ሳለ፡ ሁላችንም የምናውቀው ተፋልመን መሞት እንጂ በወቅቱ የሚደረገውን የሚመራ አዛዥና የሬድዮም ሆነ ምንም ዓይነት ግኑኝነት ከማንም ጋር የለንም። የባሕር ሃይል መደብ ዘመቻ መምሪያ ከጦር መርከቦች ጋር እንደሚገናኝ እንጂ የምናውቀው በመደቡ ውስጥ ባሉት ቀጣናዎች የትናንሽ ሬድዮ ግኑኝነት እንኳን አልነበረም። አብረን ካሉት ውስጥ የተረፍነው ወደኋላ በማፈግፈግ ለተኩስ የሚያመች ቦታ መያዝ ብቻ ነበር አማራጩ፡ በመጣንበት አቅጣጫ ዚግዛግ በማፈግፈግ ከሲናይ በላይ ባለው ግቢ አጠር ያለ የግንብ አጥር ስለነበር፡የያዝነው መትረየስ ጥይት ስለሌለው፡ ያገኘነውን ክላሽንኮቭ ጠመንጃ በመያዝ ከሌሎች ጓደኞች ጋር ተገናኘን፡ አሁንም በሕይወት አለ፡ ፒኦ ክፍሌ ወርቅነህ ካለው ጥይቶች የመጨረሻ አስር ጥይቶችን እንዳካፈለኝና የመጨረሻ የካቲት 4 ቀን ከጠላት ጋር የተፋለምንበት ቦታ ነው።

ባለን ጥይት በዚህ ቦታ ላይ ልንታኮስ የምንችለው በቅርብ ርቀት ጠላት ከፊታችን ማጥቃት ያደረገ ከሆነ ነው፡ ብለን ግንቡ ስር እንዳደፈጥን፡ ጎን ለጎን በመሆን ፊት ለፊታችን ያሉትን ለመቃኘት ለማለም ስንዘጋጅ የማያቋርጥ ተኩስ ከጠላት ተከፈተብን። የግንቡን ጫፍ እየጨረፈ ወደተለያየ አቅጣጫ የሚፈናጠረው ጥይት አንድ የምድር ጦር አባል ቀና እንዳለ ተመታና ወደቀ ተኩሱ ቀጥ እንዳለ ቀና ብለን ስንመለከት ከፊታችን ምንም እንቅስቃሴ የለም። በርቀት ለመቃኘት በየአቅጣጫችን እየተመለከትን ሳለ የውቶአማቲክ ውርጅብኝ ከጠላት እነደተጀመረ ከመሃላችን የ1982 ምልምል መርከበኛ የሆነ ወገናችን ተስዋብን የተመታው በግንባሩ ስለነበር በጥቂት ሰኮንዶች ጊዜ አረፈ። እዚያው ቤት እግቢ ውስጥ ሆነን የመጨረሻውን ውጊያ ለማድረግና ምን ማድረግ መወሰን እንዳለብን እንኳን በቂ ጥይትና የመዋጊያ አመቺ ቦታ የለንም። ምን እናድርግ ብሎ መወሰን የማይቻልበት ምክንያት፡ ከኋላችን ያለው በ300 ሜትር ርቀት ያለው ባሕር ብቻ ነው። ሰብ ሌፍትናንት ዳኜ እዚያ ጋር ብሎ እንዳመለከተን እኛ ካለንበት ማዶ ሲርመሰመሱ እንዳየን የነጠላ ተኩስ(SINGLE FIRE) ጀመርን በቀረችን ጥይቶች፡ ኢላማ ሳይሳት ለመምታት እየጮህን መነጋገርና ቀደም ብሎ ወደኛ አቅጣጫ የሚገሰግሰውን ከፊት ያለውን መባባል ሁሉ ጀምረናል። ስማቸውን የማላስታውሰውና አንዱ ፍቅሬ የሚባል የባሕር ኃይል ሙዚቀኛ ባልደረባ ቀጥሎ ባለው ግቢ አጠገብና አነስተኛ ምሽግ ውስጥ የነበሩት አባሎችም ወደምንተኩስበት አቅጣጫ መረባረብ ጀምረዋል።  ይኽ በእንዲህ እንዳለ ከኋላችን ወደሰሜን አቅጣጫ ኃይለኛ ፍንዳታና ተኩስ ተሰማን። ከኛ በላይ በስተቀኝ ከወደ ስፖርት ሜዳው አካባቢ ጠላት በታንክና እግረኛ ማጥቃት አድርጎ ኖሮ፡ የጠላት ታንክ በዋርድሩም አካባቢ ካለው የመዋኛ ገንዳ አጠገብ በመሆን ለካስ ለሊቱን LANDING CRAFT(ምድረነክ ጦር መርከብ) 1035 መዋኛው ገንዳ ፊት ለፊት ገብታ የባሕሩ ጥልቀት ቀንሶ ነበርና ሙሉ በሙሉ መሬት በመንካቷ የባሕር ጥልቀት እንደአየር ንብረት ተለዋዋጭና ጥልቀቱ የሚቀንስበትና የሚጨምርበት ጊዜ ወይም ሰአት ስላለው መርከቧ ቀዝፋ ወደመሃል ባሕር መውጣት አልቻለችም። በአካባቢው የነበሩትን የሰራዊቱን አባላትና በዘመቻ መምሪያ የነበሩትን ሁሉ ጭና ነበር። የጠላት ታንክ መሪ ክፍሉን ስለነበር የመታው ፍንዳታው እንደተሰማ ውጊያው ከወደ ጀርባችን እንደሆን ወዲያው ገባንና ዚግዛግ በመራመድ በቀጥታ ፓይሮ የሚባለው የጥይት ማከማቻ አነስተኛ መጋዘን አጠገብ ስንደርስ ውስጡ የነበረው ጥይትና ፈንጂ ሙሉ በሙሉ ወድሞና ወደግራ አቅጣጫ ስመለከት 1035 በድጋሚ ሲተኮሳባትና በላይዋ ላይ የነበሩት አባላት የሕይወት ማዳኛ ጀልባውን እንደወረወሩት በላይዋ ላይ በመሳፈር የእጅ ቀዘፋውን ተያያዙት። አንዳንዱም እየዘለለ ወደባሕር እየገባ ዋናውን ወደመሃል ባሕር ቀጠለ። በመጣሁበት አቅጣጫ ወደ Engineering WorkShop አካባቢ ሳመራ ከተለያዩ ክፍል ያሉ ወገኖች ተዳክመውና እንኳንስ ለመታኮስ ለመዋጋት የያዙትን ጠመንጃ መያዝ እንኳን ኃይል እንዳልነበራቸው ከራሴ ጭምር ምንጊዜም የማይረሳኝ ሁኔታ ነው። የመሬቱን አቀማመጥ አካባቢውን ለሚያውቅ በንባብ ሊረዳው ይችላል። የባሕር ኃይል መደብ በባሕር ወለል ልክ ያለና ለጠላት ከባድ መሳሪያ የተመቻቸ የባሕር ዳርቻ ነው። ሻቢያ ከፊት ለፊት ባሉት ከዶጋሊ ጀምሮ በአካባቢው ኮረብታዎች ላይ የረጅም ርቀት 130 ሚሜ መድፍና ቢኤም ሮኬቶችን እነድጉድ ቢያወርድም ለ3 ቀን ተኩል ያደረግነው ፍልሚያ እራስቸውም ማጥቃት ስለገቡ የሰው ኃይላቸው እንደተመናመነና፡ በኋላም 27ኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ ለቆ ለእርዳታ በመጣበት አቅጣጫ በፎሮ በኩል የሕወሃት ወያኔ እግረኛ ጦር በአዲስ ጉልበት የባሕር ኃይላችን መደብ ላይ ደክሞና ዝሎ ያለምንም ቀያሪ ጦር መንቀሳቀስ እንኳን ከተሳነው ጀግናው ሰራዊት ጋር በመፋለም ግቢያችንን ተቆጣጥሮ ለሻቢያ አስረከበው።

የምድረነክ ጦር መርከብ መመታትና ካለንበት ፓይሮ በላይ በጠላት እጅ ስለወደቀ አጠገቤ ከነበሩት ጋር በመሆን ተኝተን እንዳደፈጥን፡ የአየር ኃይላችን ከባሕር ወደምጽዋ ባሕር ኃይል መደብ በመብረር በግቢያችን ውስጥ ያለውን የሞቢል ነዳጅ ማጠራቀሚያ ጋን ጠላት እንዳይጠቀምበት ቦምብ ሲያወርድበት ካለንበት ቦታ ላይ የወደቀ ይመስል የመሬቱ ንቅናቄ አካባቢውን አናወጠው።

አሁን ማድረግ ያለብን ከኋላችን ያለው ባሕር ብቻ ስለሆነ በዋና ወደወደቡ ጫፍ ርእሰምድር ደረስን። ርእሰምድር እንደደረስን አንድ የ6ኛ ክፍለጦር ጤና ረዳት፡ ከነጫማዬ በተረከዜ አካባቢ ቀላል የተመታሁበትን በማየት የመጀመሪያ እርዳታ አደረገልኝ ለክፉ የሚሰጥም አልነበረም። የእግረኛ ውጊያ የባሕር ኃይል እንደዚህ ይዋጋል ብለን አልጠበቅንም ነበር፡ በጣም የሚደነቅ ተጋድሎ ነው ብሎ እንደተናገረ፡ እንደኔው ተርፈው እዚያ የተገናኘን አባሎች ጋር በመሆን ጀግናው ኮሎኔል በላይ አስጨናቂ ጋር ሄደን አመለከትን። እንዲህ ነው የኔ ልጆች፡ የባሕር ኃይላችን አባላት በዚያች አነስተኛ ግቢ ያለእረፍት፤ያለማቋረጥ ማድረጋችሁ የሚደንቅ ነው። ጦርነቱ 1 ለ10 ሆኖ እኮ ነው ነው ሲሉን አልገባንም ነበር። ሻቢያ በደንጎሎና አርብሮብና አለፍ ባሉት ቦታዎች ላይ ይወገን ጦር ለእርዳታ እንዳያልፍ የመድፍ ድብደባ ያለማቋረጥ እያደረገ ስለሆነ ቦታው በግራም በቀኝም ገደልና በውጊያ ተዋግቶ ለማለፍ አይቻልም፡ ያለምንም እግረኛ ጦር መድፍ በመተኮስ ብቻ መቆጣጠር የሚቻል ቦታ ነው ሲለን፡ መንገዱንና ቦታውን ስላየሁት በርግጥም አሳማኝ ሁኔታ ነው።

እዳጋ ከተማ ጫፍ ከሲኒማ ቤቱ እስከ ጥዋለት ሰፈር ምጽዋ ከተማን የሚያገናኘው ድልድይ መሠረቱ ባሕር ውስጥ ተቀብሮ የተሰራ ኮንክሪት ድልድይ ጫፍና ጥዋለት ማርያም ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት የ27ኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ 6ኛ ክፍለጦር መሸገው ሻቢያ አራት(4) ጊዜ በተደጋጋሚ ሰብሮ ለመግባት የላካቸውን

አራቱንም ታንኮች አቃጥለውና አውድመው በሞራል እየተዋጉ ሳለ ኮሎኔል በላይ፡ አንድ የምድር ጦር መኮንን የሰው ኃይል ስለሚያስፈልገን ከባሕር ኃይል መደብ የተረፉትን አባላት ተጨማሪ አድርገን ጥዋለት እንውሰዳቸው የሚል ሃሳብ ለኮሎኔል በላይ ሲነግራቸው፡ ያለምንም እረፍት ሲዋጉ ተዳክመዋልና፡ ተውዋቸው አሉና፡ በአጋጣሚ ደረጀ የሚባል CRYPTOMAN(RADIYOMAN) በመደቡ ዘመቻ መምሪያ ሬድዮ ክፍል የሚሰራ ከምድርጦር ሬድዮማኖች ጋር ተነጋግሮ ከጦር መርከብ ኢትዮጵያ ጋር ተገናኝቶ ባላችሁበት ቆዩና የባሕር ጠለቅ ኮማንዶ አባላት ወደመርከብ ያመጧችኋል የሚል መልእክት ደረሰን። በማግስቱ ተንቀሳቀሱ ተብለን ወደጥዋለት በአንዲት ቶዮታ መኪና ከሳቮያ ወደጥዋለት አመራን። እንኳንስ ልንዋጋ በወቅቱ የያዝነውን ጠመንጃ እንኳን መያዝ ያቃተንን፡ ለ5 ቀናት ደረቅ ራሽንና ውሃ እንኳን ያላገኘንና የተዳከምን ሆነን ሳለን፡ አንድ የምድር ጦር መኮንን ጥይት የእጅ ቦምብና ጠመንጃ አድሎን እዚህ ሆናችሁ የጠላት ታንክም ይሁን እግረኛ ከመጣ ተጠቀሙበት ብሎን ወደመጣበት አቅጣጫ ሄደ። ሁኔታው ግራ የሚያጋብ ስለሆነብን ወደጥዋለት ወዳሉት ወታደሮች ስናመራ፡ ጠላት ሰብሮ ለመግባት ሲሞክር 4 ታንኮችን ማቃጠላቸውን ሰማን። የሚቀመስ ነገር ለመንቀሳቀስና ሃይል ማግኘትም አስፈላጊም ነበርና እንዲሰጡን ስንጠይቅ መልስም የለ ምንም የለም። በአጋጣሚ ሆኖ፡ የባሕር ኃይል ሲቪል ሰራተኛ የሆኑት አቶ ብሩኖ ጂያኮሞን ማዳም ሜሎቲ ግቢ አጠገብ አግኝተናቸው በጣም አዘኑና እነማን ተረፉ እነማንስ አረፉ ሲሉኝ፡ኣይይ አሁን ምንም ለማወቅ አይቻልም፡ እባክዎን የሚቀመስ ፈልጉልን ስንላቸው ብዙሃን ቤተሰብ ከመሸጉበት የማዳም ሜሎቲ ግቢ ከህዝቡ ጠይቀው አመጡልን፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ከ5 ቀናት በኋላ ምግብ በአፋችን ተቀመሰና፡ የምናደርገው ግራ አጋብቶንና እንዲህ አድርጉ የሚል ተባባሪ በማጣታችን ሁኔታ ሳለ፡ የባህር ኃይል መደብ አዛዥ በዚያን ወቅት ኮማንደር በኋላም ካፒቴን ተስፋዬ ከበደን ከጄኔራል ተሾመ ጋር አገኘናቸው። ጠላት ወደ ጥዋለት ሰብሮ ለመግባት ሲሞክር፡ ካፒቴን ተስፋዬ ከበደ ባሕር ላይ ካሉት ጦር መርከቦች ጋር እየተገናኙ በባሕር ላይ ተቀብሮ እዳጋና ጥዋለትን የሚያገናኘውን ድልድይ እንዲደበደብ በማድረጋቸው ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገው ነበር። በምድረነክ የጦር መርከብ ተጭነው የመጡት የምድር ጦር አባላት አረንጓዴ ደሴት በሚባለው በምጽዋ ከተማ በስተኋላ ከዳንስ ማሪያ አቅጣጫ ወታደሮቹን ለማውረድ ስትጠጋ፡ ማዳም ሜሎቲ ግቢ በስተጀርባ ከጥቂት የባሕር ኃይል አባላት ጋር ስንመለከት ከወደ አጂፕ ነዳጅ ማከማቻ ወይም በሕርጊጎ ባህር ማዶ ሁለት የጠላት ታንኮች ከባህሩ ጠረፍ ላይ ሆነው መተኮስ ጀመሩ፡ አንድ ጥይት ጭርፏት ሲሄድ እንዳየን፡ አይ አየር ኃይላችን! እንዴት ኢላማውን እንዳገኛቸውና ሰማዩን ሁሉ በአየር መቃወሚያ የሞላውን ፍንዳታ በማለፍ ሁለቱም ታንኮች መሃል፡ ፓራሹት ቦምብ እንደለቀቀባቸው ሲቃጠሉ በአይናችን ያየን ሲሆን፡ ምድረነክ የጦር መርከብም የጫነቻቸውን ወታደሮች ለማውረድ ባለመቻሏ ወደመሃል ባሕር ቀዘፈች። ካፒቴን ተስፋዬ ከበደም በጄኔራል ተሾመ ተሰማ ጂፕ መኪና ወደምጽዋ ከተማ በመሻገር በ1036 ወደባህር ወዳሉት መርከቦች መቀላቀላቸውን ሰማን።

በማግስቱ ሻቢያ ሰብሮ ለመግባት ሲሞክር፡ ጄኔራል ተሾመ ያሉት ነገር፡ ያ ኮማንደር አብሮኝ ቢሆን ኖሮ ልክ እንደሰሞኑ ጥዋለትንና እዳጋን የሚያገኛናኘውን መሰረቱ ሙሉ በሙሉ ባህር ውስጥ ተቀብሮ የተሰራውን ድልድይ ታንኮችና ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች እንዳያልፉ ያስደበድብልኝ፡ብለው እንደነበር አብሮኝ፡የነበረው የባሕር ኃይል ሙዚቃ ክፍል ባልደረባ ፒ/ኦ ሰለሞን ጎሩይ አጋጣሚውን አጠገባቸው ሄዶ ስለነበር ቁጭታቸውን ነግሮን ነበር።

ያ ሁሉ ተጋድሎ እንዴት እንደነበር “ አይ ምጽዋ “ በሚል ርእስ በ50 አለቃ ታደሰ ሳልቫኖ በግልጽ የቀረበ ሲሆን በመጽሓፎቹ ገጽ በገጽ ስህተት ነው የምለው:-

1ኛ- በገጽ 132 ሶስተኛው አንቀጽ “ አየር ኃይል በባህር ኃይል መደብ ላይ የጣለው ቦምብ መሬት ደርምሶ ውሃ አወጣ እንጂ ወይም በሻቢያ ላይ ከባድ ድንጋጤን ፈጠረ እንጂ የፈየደው ነገር የለም ይላል ጽሁፉ፡ ነገር ግን ቦምቡ የተጣለው በነዳጅ ማከማቻው ጋን ላይ እነደመሆኑ ጠላት ነዳጁን እነደነበር ካገኘ ለታንኮቹም ይሁን ለሌላ ተሽከርካሪዎቹ እንዳይጠቀምበት ያስደበደቡት ካፒቴን ተስፋዬ ከበደ ናቸው። በግቢው ውስጥ ያለ ነገር ጠላት እንዳይጠቀምበት እርምጃ መወሰዱ ወታደራዊ ስትራተጂ ነው።

2ኛ- በገጽ 163 ያለው ፎቶግራፍ በዘመነ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ባሕር ኃይል ምጽዋ ወደብ ላይ በመርከብ የሚመጡትን የውጭ ሃገር እንግዶች ለመቀበል የተነሳ የክብር ዘብ ፎቶግራፍ እንጂ የባሕር ኃይል መደብ አይደለም። ከበስተኋላው የምጽዋን ከተማ ማየትም ይቻላል።

3ኛ- ገጽ 162 ከምጽዋ ወደጉርጉሱም ከአማተረ አለፍ ብሎ የከባድ መሳሪያ ጥይት እንደተከማቸና በጠላት እጅ ስር እንደወደቀ ተጠቅሷል። ከባሕር ኃይል መደብ ወደተጠቀሰው ቦታ ጥይቶች በከባድ መኪናዎች ሲጓጓዝ በሃላፊነት ከባሕር ኃይል መድፈኛ ወርክሾፕ ተመድቤ ከሾፌሮች ጋር በመላለስ ቦታውን የማውቀው ሲሆን፡ የካቲት 1 ቀን የጦር አይሮፕላኖቻችንና MI24 ሄሊኮፕተሮቻችን አውድመውታል። ሻቢያ ከናደው እዝ ባገኘው መሳሪያ ወጋን የሚልም በአንድ ገጽ ያነበብኩኝ ሲሆን፡ ፈጽሞ ስህተት ነው። ሻቢያ ክተዋጊ አይሮፕላኖች በስተቀር፡ ከ 130 ሚሜትር መድፍና ጥይቶች፤ ታንኮችና እስከነፍስ ወከፍ ጠመንጃዎች ከአረብ ሃገራት የሱዳን ሁለተኛ ወደብ በሆነችው በገፍ ይገባላቸው እንደነበር መረጃዎች ነበሩ እንጂ፡ ከሰራዊታችን አገኙ የሚባለው፡ ቢማርኩና ቢያገኙም እንኳ በሜዳ ላይ የበሰበሰ የቆየ ጥይት ከመተኮስ ይልቅ፡ እዚያው የሚፈነዳዳ ነው።

4ኛ- በገጽ 120 እና 121፡- ከስንዴ በስተቀር ምሽግ መስሪያ ማቴሪያል የለምና ምጽዋ ወደብ በተከማቸው የእርዳታ ስንዴ ምሽግ ሰርተን አጠናክረን ሻቢያን መግደልና መደምሰስ ብቻ ነው። የሚል ገጽ 121 ላይ አንብቤያለሁ። የሚገርምና የሚያናድድ የሚያበሳጭ ሁኔታ እዚያው ርእሰምድርን እንዳለፈኩኝ BM-21 ሮኬትና ታላላቅ መድፎችን ሩሲያ ተምሮ እኛን ለሁለት ቀናት ያስተማረን ጭምር ወታደሮችን እያስተባበረ ምሽግ በስንዴ ሲሰሩ ስመለከት እንዴ ምንድነው ነገሩ እንዳንል፡ የምድር ጦር ተዋጊ ከ10- 15 ዓመታት የውጊያ ልምድ ያላቸው በእድሜም የሚበልጡን ወታደሮች ሆነው ሳለ፡ ለመናገርም አልደፈርንም። ሻቢያ የመድፍ ድብደባ ወደቡ ላይ ሲያከታታል የስንዴው ምሽግ እንደጧፍ ነዱል አይ ምጽዋ በሚለው መጽሃፍም ተጠቅሶ ስህተት መሆኑ አልተጠቀሰም።
5ኛ- በገጽ 132 ሻቢያ የካቲት 4 ቀን 1982 ዓም ከጠዋቱ 4 ሰአት ላይ ሙሉ በሙሉ የባሕር ኃይል መደብን ተቆጣጠረ የሚልም ተጽፏል፡ ቀኑና ዓመተምህረቱ ትክክል ሲሆን ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠሩት ከቀኑ ስድስት ሰአት አካባቢ ነው። በተለምዶ ሲናይ ወይም ከኮሌጅ ባራክስ ወረድ ባለው ቦታ ላይ፡ ከወያኔ እግረኞች ጋር ስንዋጋና ወደዋናው በር ማጥቃት ተብሎ ከአስከሬኖች ፍተሻ ወያኔ ተዋጊዎችን መረጃ ባገኘን ሰአት በግምት ከአራት ሰአት ተኩል በላይ ነበር።
በወቅቱ ኮሞዶር ፊሊጶስ የ NORTHERN NAVAL COMMAND( የሰሜን ባሕር ኃይል አዛዥ እንጂ የጦር መርከብ ኢትዮጵያ አዛዥ አልነበሩም። በወቅቱና የመጨረሻው የጦር መርከብ ኢትዮጵያ ዋና አዛዥ፡፡ኮማንደር ይትባረክ ዘርዓዝጊ ይባላሉ።

## ማጠቃለያ

በተረፈ የ50 አለቃ ታደሰ ሳልቫኖን “ አይ ምጽዋ “ መጽሃፍን ያነበቡ ሁሉ ከልብ የሚያመሰግኑና የባሕር ኃይል አባላት መጽሃፉን ዘግይቶም ቢሆን ስላበረከቱልኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው።
በዚያ ታይቶ በማይታወቅ ከባድ ጦርነት ጀግና ብቻ ሳይሆን የታየው፡ ፈርቶም ግዳጅን ጥሎ የኮበለለ፡ አንዲት ጥይት ሳይተኩስ በተደበቀበት ያለፈና እራሡን ያጠፋም ነበር፡፡ ከፍተኛ ምስጢራዊ ሰነዶች በየቢሯችሁ ያላችሁ ሰንዶችን የሚቃጠለውንም አቃጥላችሁ መያዝ ያለባችሁንም ይዛችሁ በጀልባዎች ወደመርከቦች ተዛወሩ ሲባል፡ ወደመርከብ የወጡም እንዳሉና ማምለጣቸውንም እንደጀብዱም የሚነገሩን አጋጥመውናል።
ለሁለት ጊዜያት የጀግኖች ምሽት በዓል በሃገር ወዳድ እውነተኛ ኢትዮጵያውያን የቀድሞው ጀግናው ሰራዊታችን ሲወደስ፡ በእውነቱ ከልብ ከልቤ የኢትዮጵያ አምላክ ይባርካችሁ ነው የምለው። ውድ ሕይወቱን ለዚህች ምስኪን ሃገርና ሕዝብ ሊሰጥ ደፋ ቀና ሲል የነበረውን ወታደራዊ ደህንነት የሚባለው ጸረ ኢትዮጵያውያን ማፍያ ድርጅት፡ የስንቱን ውድ ወገናችን ሕይወት በልቷል?
መላው ማለት ይቻላል። የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል በመንግስት ላይ አመጽና ለሃገሪቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ጥያቄ ባቀረበና ባደረገ ጊዜ፡ 11 ውድ ወገኖቻችንን ጉርጉሱም ላይ ያስረሸነው፡ በተስፋዬ ወ/ስላሴ ብቻ ነው የምታዘዘው ይል የነበረው የደኅንነቱ ኮማንደር ፍስሃ፡ በጀግኖች ምሽት ከተከበሩት የኢትዮጵያውያን ወታደሮች ስም ዝርዝር ሲያቀርቡት ወዲያውኑ ወደአሜሪካ በመደወል ከአዘጋጆቹ አንዱን የአየር ኃይል ባልደረባ ሳናግር፡ ያገኘነው፡ ከባሕር ኃይል መጽሃፍ ነው ሲሉኝ በወቅቱ መጽሃፉ በእጄ ባይገባም፡ ተቃውሞዬን በጽሁፍ አቅርቤ ነበር። ለሁለተኛ ጊዜም ከንጹሃን ስም ጋር የኮማንደር ፍሥሃን ስም ሳነብ፡ የሚታወሰኝ፡ አብሮኝ በባሕር ኃይል አባልነት ተቀጥሮና በእድሜያችን ገና የ19 ዓመት ሳለንና ከባሕር ኃይሉ የመጨረሻ ጁኒየርና ተለማማጅ ባሕረኛ ሳለን“ ORDINARY SEAMAN አማረ እሸቱን ከነባር ምስኪን የባሕር ኃይል አባላት ጋር ኮማንደር ፍስሃ አስረሸናቸው። በምጽዋ ውጊያ፡ ኮማንደር ፍስሃ GUST HOUSE በሚባለው ቤት ውስጥ እንደመሸገ እዚያው ነው የቀረው። በምጽዋ ባሕር ኃይል መደብ ደህነንት የመመርመሪያና የመግረፊያ የማሰቃያ ቢሮ ነበረው።
በግንቦት 1981 ዓም መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተደርጎ በነበር ጊዜ፡ መፈንቅለ መንግስቱን በመደገፍም ሆነ በማውገዝ ከተጠሩት ብዙኃን ውስጥ ነበርኩኝ። ታላቅ ምስጋና ለሪር አድሚራል የኋላሸት፡ ደህንነቱንም ሆነ የፖለቲካ መምሪያውን አስታግሰውልን፡፡ ለድል ባንበቃም ምጽዋ ላይ ያደርግነው ተጋድሎ በምጽዋ ጦርነት መጽሃፉን ከታሪክ አኳያ አስተማሪነት ቢኖረውም ከምጽዋ ጦርነት በፊት ያገለገልኩባቸውን ሁለቱን የባሕር ኃይላችንን 201-ኛውን ፈጣን ተዋጊ የጦር መርከብና 111ኛውን ፈጣን አጥቂ የጦር መርከብ ትዝታና ግዳጃችን እንዴትና OUTSTANDING የጦር መርከብ አዛዦቻችንን ትሩፋት፡ በሚቀጥለው ደግሞ በቅርቡ የባሕር ኃይላችን ማሕበርተኞች ካሳተሙት መጽሃፍ አስተያየቴን ለማቅረብ እሞክራለሁ።
አስተያየት ለምትሰጡኝ አድራሻዬ፡- fggebreyes2@gmail.com

ክብር ምስጋና ለአምላካችን እግዚአብሔር ይሁንልን።«First Name» Fresenay Kebede